# ‹ሕግን የሚተው ሰዎች ኀጥአንን ያመሰግናሉ፤ ሕግ ጠባቂዎች ግን ይጠሉአቸዋል፡፡›

(መጽሐፈ ምሳሌ፤ ምዕ. 28 ቁ. 4.)

በሚያዝያ 5 ቀን 1998 ዓ.ም. ምሽት በአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ የአማርኛው ስርጭት ላይ የአሜሪካ ጉዳይ ፈጻሚ በኢትዮጵያ ቀርበው ኢትዮጵያን በተለይም ቅንጅትን በሚመለከት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ሲሰጡ አዳመጥን፡፡ ስናዳምጥም በጉጉትና በአንክሮ ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ በረጅሙ ከጠቀሱት የመጽሐፈ መክብብ ማጠየቂያና በኒልሰን ማንዴላ ሞዴልነት ያቀረቡት ማብራሪያ ኢትዮጵያ ለምትገኝበት ተጨባጭ ሁኔታ የሚመጥን ሳይመስለን ቀረ፡፡ እንዲያውም ለማገናኘት እንኩዋን ብንሞክር የሚገናኙበት አንዳችም ተጠየቃዊ መስመር እንደሌለ ገባን፡፡ በዚህም የተነሳ ይህችን መጣጥፍ ልንጫጭር በቃን፡፡

ውድ ወገኖቻችን፣ የማይሆን ነገር እያገባጠሙ የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያውያንን ችግር፣ አበሳና ስቃይ የሚያባብሱ ሰዎች ቁጥራቸውና ውገናቸው ከማን እንደሆነ ከገባን ውሎ አድሩዋልና በዚህ በኩል የምንታለል ኢትዮጵውያን እንኖራለን ብለን አንሰጋም- አውቀን ካልተኛን በስተቀር፡፡

> መጀመሪያ፣ ጉዳይ ፈጻሚዋ ወደጠቀሱት የመጽሐፈ መክብብ ምሳሌ ልመለስ፡፡ "ለሁሉ ዘመን አለው፣ ከሰማይ በታች ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው፡፡ ለመወለድ ጊዜ አለው፣ለመሞትም ጊዜ አለው፤ ለመትከል ጊዜ አለው፣ የተተከለውን ለመንቀል ጊዜ አለው፤ ለመግደል ጊዜ አለው፣ ለመፈወስም ጊዜ አለው፤ ለማፍረስ ጊዜ አለው፣ ለመስራትም ጊዜ አለው፤ ለማልቀስ ጊዜ አለው፣ ለመሳቅም ጊዜ አለው፤ ዋይ ለማለት ጊዜ አለው፣ ለመዝፈንም ጊዜ አለው፡፡..." (መክብብ፣ 3፣ ከቁ. 1እስከ 8 ይመልከቱ)፡፡

ከዚህ ጥቅስ የተረዱትን ሊያስረዱን ፈልገው ይመስለናል የጠቀሱልንና እኛ የገባንንና የምንገነዘበውን ያህል ሀሳባችንን እናቅርብ፡፡ ጥቅሱ እንደሚናገረው ለእያንዳንዱ ነገር ሁሉ ጊዜ እንዳለው እንጂ ጊዜ እንደሌለው አይደለም፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ለመመስረት ጊዜ ያስፈልግ ነበር፤ አዎ እስከ አምና ግንቦት ሰባት ድረስ ጊዜ ወስዶ ነበር፡፡ ግንቦት 7 1997 ዓ.ም. ግን የዲሞክራሲ ግንባታ መሠረት የተጣለበት አቅዋመ ማዕዘኑ የተተከለበት ቀን ነበር፡፡ ጊዜው መድረሱንና መብቃቱን ያልተገነዘቡ አማፅያንና አጫፋሪዎቻቸው ‹እምቢ- አሻፈረኝ!› አሉ፤ ዲሞክራሲ ለመወለድ ጊዜ ነበረውና ግንቦት ሰባት ተወለደ፤ አለጊዜው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በዕለቱ ዕለት በአዋጅ አንቀው ሲጥ አደረጉት! ገደሉት! ዲሞክራሲ ጊዜው ደርሶ ግንቦት ሰባት ተተከለ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ አለጊዜው በዕለቱ ነቀሉት! መነገሉት! የፈውስ፣ የመስራት፣ የመሳቅ፣ የመዝፈን … ጊዜዎች አምና ግንቦት ሰባት 1997 ዓ.ም፣ ተፈጽመው ነበር፤ ጠቅላይ ሚኒስትር በዕለቱ ዕለት የመግደል፣ የማፍረስ፣ የማስለቀስ፣ የዋይታ፣ … አዋጅ አወጁባቸው፡፡ ሁሉም ለኢትዮጵያ የሚበጅ ነገር በጊዜው ሆኖ ነበር፤ የሥልጣን ዘላለማዊነት በልባቸው የተተከለባቸው፣ በአእምሮአቸው የተደነቀረባቸው ጠቅላይ ሚኒስትርና አጫፋሪዎቻቸው እንዳይሆን አደረጉት፤ አፈረሱት፤ ናዱት፤ ሰላማዊ ዲሞክራሲያዊ ሂደቱን እንቅሽቅሹን አወጡት- አወደሙት!

ከዚህ በሁዋላ የሆነው ነገር ሁሉ የዚያ ዲሞክራሲያዊ ሂደትንና ፍጻሜን ለማውደም የተወረወረ ጦርና የተረጨ መርዝ ውጤት ነው፡፡ ህዝብ በዲሞክራሲ አምኖ መረጠ፤ ድምጹ ተሰረቀ፡፡ ድምጼን ፣መልሱ ብሎ ጮኸ፤ ለጩኸቱ የተሰጠው ምልሽ እንግልት፣ ድብደባ፣ እስር፣ ግድያና መሳደድ ሆነ!

የአሜሪካዋ ጉዳይ ፈጻሚ ይህንን ዘንግተው ሳይሆን በምን ቸግሮኝ ባይነት-ማለትም የተንገላቱ ኢትዮጵያውያን፣ የተደበደቡ ኢትዮጵያውያን፣ የታሰሩ ኢትዮጵያውያን፣ የተገደሉ ኢትዮጵያውያን፣ የተሳደዱ ኢትዮጵያውያን እንጂ አሜሪካውያን ስላልነበሩና ስላልሆኑ ለሁሉም ጊዜ አለው አሉን። ጊዜው ደርሶ ለነጻነቱ ድምጽ በሰላማዊ መንገድ የሰጠውንና በዘራፊዎች የተነጠቀውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲን ለመትከል ጊዜ አለው አሉት። አዎ! ጊዜ ስላለውና ስለደረሰማ ግንቦት ሰባት ዘጠና ሰባት መሪዎቹን መርጦ ዲሞክራሲን ተክሎ ነበር! አይሠሩ ሥራ ተሠራ እንጂ!

እሳቸው የጠቀሱት መጽሐፍ ዝቅ ብሎ በምዕ. 7 ላይ ከቁ. 7 ጀምሮ "ግፍ ጠቢቡን ያሳብደዋል፤ ጉቦም ልቡን ያጠፋዋል። የነገር ፍጻሜ ከመጀመሪያው ይሻላል፤ ታጋሽም ከትዕቢተኛ ይሻላል። በነፍስህ ለቁጣ አትቸኩል፣ ቁጣ በሰነፍ ብብት ያድራልና።" ይላል። ይህንንም ጨምረው አንብበው ትእግስት ከማን እንደሆነች፣ ስንፍናና ቁጣ ደግሞ ከየት እንደሆነች፣ እንዲሁም ጉቦና ሙስና ከነማን ዘንድ እንዳለች አብረው ቢገነዘቡልን እንዴት በበጃቸው ነበር።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ምን አደረገ ተብሎ ነው- እየተገደለ፣ እየታሰረ፣ ንብረቱ እየተዘረፈ፣ ከሥራ እየተፈናቀለ፣ እየተባረረ፣ እየተደበደበና እየተሳደደ ያለው? መጽሐፈ መክብብ አሁንም ዝቅ ይልና እንዲህ ይላል። "ትዕግስት ታላቁን ኃጢአት ጸጥ ያደርጋልና የገዢ ቁጣ የተነሳብህ እንደሆነ ስፍራህን አትልቀቅ። ከፀሐይ በታች ያየሁት ክፉ ነገር አለ፣ እርሱም ከገዢ የሚወጣ ስህተት ነው፤... " (ምዕ. 10. ከቁ. 4 እስከ 6)

እሺ ኢትዮጵያውያን ከዚህ የተለየ ምን ሆኑ? ምንስ አደረጉና ታሰሩ፤ ተገደሉ? ሰብአዊነት ሲነፈጋቸው፣ ዲሞክራሲያዊ መብታቸው ሲነጠቅ፣ እንደ ህዝብ ሳይሆን እንደ መንጋ ሲታዩ፣ እናንተ ያላችሁት፣ ያመናችሁበት ሳይሆን እኔን የሚመቸኝን ተቀበሉ የሚል ዘራፊ መንግሥታዊ ሽብርተኛ ሲገጥማቸው ከመታገስና በሰላማዊ ሁኔታ ከመታገል ውጪ ምን እንዲያደርጉ ይፈለግ ነበር? የገዢ ቁጣ የተነሳብህ እንደሆነ ስፍራህን አትልቀቅ እንጂ ተሰደድ፣ ተሳደድ፤ ታሰር፣ ሙት፤ እኮ አላለም።

ከቃለ መጠይቁ ውስጥ የገባኝ ዲሞክረሲን ለማምጣት የሁሉም ወገን ተሳትፎ አስፈላጊ መሆኑ ነው። ይህ የሚያጠያይቅ አይደለም። የሚያስጠይቀው ግን ሁሉም ሲባል የሚያቅፈውና የሚያንገዋልለው አካል የኖረ እንደሆነ ነው። ምክንያቱም ሌላውን የአገሪቱን ነዋሪ እንኩዋን ትተን የአዲስ አበባን ህዝብ ድምጽና መብት ብንይዝ እንዳለ እኮ የተረገጠ፣ የተጨፈለቀ ነው። ተመራጮች ታስረዋል፤ ተደብድበዋል፤ ተሳድደዋል፤ ታፍነዋል፤ እየተዋከቡ ነፍስና ስጋቸው እለት በእለት እየተጨናነቀች፣ በስጋትና በፍርሀት ተወጥረው ይገኛሉ። ይህንን ደግሞ የአሜሪካ ጉዳይ ፈጻሚ በሚገባ ያውቃሉ። በዚህ የነፍስ ውጪ- ግቢ ውስጥ ሁሉ ሰላማዊ ተመራጮችና የሕዝብ እንደራሴዎች ባሉበት ሁኔታ እንዴት ተደርጎ ነው በዲሞክራሲያዊ ሂደቱ ሁሉም የአገሪቱ ዜጎች፤ ሁሉም የዲሞክራሲ ተቋማት፣ ሁሉም የሲቪል ማህበራት አስተባባሪዎችና መሪዎች ሊሳተፉ የሚችሉት? ገጣሚው እንዳሉት፡-

እያነፈነፈ እንደውሻ እንዲሮጥ፤
ሰውነቱን፣ ክብሩን በሆዱ እንዲለውጥ፤
ሰው አልተፈጠረም፤ እንዲኖር በቅልውጥ! (መ.ወ.ማ. ገጽ 10)

መሆኑ ቀረና አንዳንድ አጎብዳጅና ሆድ አዳሪ ተመራጭ ነን ባዮችን እየነጠሉ ‹እሺ› ያለውን በጥቅማጥቅም በመደለል፣ ‹እምቢ› ያለውን ደግሞ በየጉዋዳውና በየስርጉዋጉጡ እያስፈራሩ፣ እውነተኛ ዲሞክራሲያዊ ህይወትን ማስፈን ይቻላል ወይ? ‹ጻድቃን በበዙ ጊዜ ሕዝብ ደስ ይለዋል፤ ኀጥአን በሠለጠኑ ጊዜ ሕዝብ ያለቅሳል›

( ምሳሌ፤ ምዕ. 29፣ ቁ. 2) በእኛ አገር ኢትዮጵያም ሆነ በአለም ድሀ አገሮች ይህ ሀቅ አይደለም ወይ ያለው? ኢትዮጵያውያን ጨቋኞችና ጎጥአን በህዝብ ጫንቃ ላይ ሰልጥነውና ተንደላቅቀው በሚገኙበት እውነት ውስጥ አይደለንም ወይ? ይሄ እንዴት አይታይ -አይታወቃችሁም?

ሕጻናትን በየትምህርት ቤቱ ደጃፍ የሚገድሉ፣ ሚስትን በልጆችዋና በባልዋ ፊት የሚረሽኑ፣ የቤት እመቤት፣ የሰባት ልጆች እናትና የአሥር ልጆች አሳዳጊ የሆኑ ባልቴት በአደባባይ እበራቸው ላይ የሚደፉ፣ በየአደባባዩ፣ በየመጓጓዣው፣ በየምግብና መጠት ቤቱ ውስጥ ፈንጂ እየቀበሩና እያፈነዱ፣ በግለሰብ ቤት፣ ኪስ ወይም ቦርሳ ውስጥ፣ ቦምብ እያኖሩ ይህ ያንተ ነው የሚሉ ዓይን አውጣ አምባገነን አውሬዎች ባሉበት አገር ውስጥ እምንገኝ መሆናችንን አላውቅም ሊሉን፣ ሊክዱን፣ ካልፈለጉ በስተቀር እንዴት ነው ሁሉም ወገን የሚሳተፍበት ዲሞክራሲያዊ ሂደት ሊኖር የሚችለው? ይህን ማለቂያ የሌለው ጥያቄ እዚሁ እንተወውና ወደሌላው ነጥብ እንለፍ፡፡

ሁለተኛው ነጣባችን የማንዴላ ምሳሌነት ነው፡፡ ማንዴላ እስርቤት እያሉም ትግሉ አልቆመም ነበር፤ ከእስርቤት ሲወጡ ተገቢ ቦታቸውን አግኝተዋል፤ የሚል አንድምታ ያለው ማጠየቂያ አቅርበዋል፡፡ ለመሆኑ የማንዴላን ብሔራዊ ኮንግረስና የደቡብ አፍሪካን አፓርታይድ አገዛዝ ከእኛ ሁኔታ ጋር በየት አዙዋዙረው አገናኙት? የማንዴላ የአፍሪካ ብሔራዊ ኮንግረስ በህግ ያልተፈቀደለት፣ ለነጻነቱ ለመታገል ያመቸኛል ያለውን ሁሉ የትግል ስልት ይጠቀም የነበረ፤ የእኛ ደግሞ ‹በሰላማዊ ውድድር ብቻ ታግለንና ተፎካክረን ዲሞክራሲያዊ መብታችንን እናስከብራለን፤ ደም ማፍሰስ፣ ሕዝብ መጨረስ ይብቃ› ብለው በህግ ተቋማትና በአደባባይ ታውቀው ይንቀሳቀሱ የነበሩ፣ እንዴት ሆነው ነው ሊነጻጸሩ የሚችሉት? ማንዴላ ታስረው እኮ ድርጅታቸው በተለጣፊና በከሀዲ ሌላ ድርጅት አልተተካም፤ ወይም ሊተካ አልተሞከርም፤ እሳቸው እስርቤት ሆነው ሌሎች በህቡዕ ያሉ የድርጅቱ መሪዎችና ህዝቡ እኮ ትግላቸውን አላቋዋረጡም ነበር፡፡ (ልክ አሁን ኢትዮጵያውያን እንደምናደርገው ድምታችን ይከበርና መሪዎቻችን ይፈቱ የሚል ሰላማዊ ትግል ባይሆንም!) የደቡብ አፍሪካ አፓርታይድ ገዢዎች እኮ ለሃያ ሰባት ዓመታት ማንዴላን ያሰሩበት ምክንያት ማንዴላ ሲፈቱ ስልጣን ለማስረከብ ብለው አልነበረም- የህዝቡን የነጻነትና የመብት ጥያቄ ለማዳፈን እንጂ!

በኢትዮጵያ የቅንጅትን ዋና ዋና መሪዎችንና የህዝብ እንደራሴዎችን በእስር ቤት አጉሮ ተለጣፊ ቅንጅት ለማቋቋም ላይ ታች ሲባል በደቡብ አፍሪካ ያለው በጨካኝነቱና በጨቋኝነቱ ወደር ያልነበረው የአፓርታይድ አገዛዝ ተለጣፊ ኤ. ኤን. ሲ አልፈጠረም፡፡ ስለዚህ ማንዴላን ከአሁኑ የኢትዮጵያ ጉዳይ ጋር የሚያያይዝ አንዳች ተጠየቃዊ ምክንያት የለም፤ ‹ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ› እንዲሉ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ቅንጅትን በእሥር ቤት ከሚማቅቁት መሪዎቹ ነጥሎ እንደማያይ ሁሉም በማያሻማ መልኩ ሊረዳው ይገባል፡፡ ቀድሞውንም ሕዝቡ የቅንጅትን ተወዳዳሪዎች ሲመርጥ አንቱ በተባሉ መሪዎቹ ዓይንና ድርጅታዊ ብቃት አንጻር አይቶ እንጂ አንዱን ዕጩ ተወዳዳሪ ከአንዱ ጋር በግል እያወዳደረና እያነጻጸረ እንዳልነበር ለማንም ጆሮና ጭንቅላት ላለው ሰው ግልጽ ነው፡፡ እምነቱን በእነዚያ መሪዎች አጠቃላይ ቃልና ተግባር ላይ ጥሎ እንጂ እያንዳንዱን ግለሰብ በግላዊ ባህሪው እየመዘነ አልነበረም፡፡ በመሪዎቹ ላይ በነበረው ጽኑ እምነት መሠረት ምንም ቢሆን ከንቱና ሆዳም፣ አታላይና ከሃዲ ሰዎችን ለፓርላማም ሆነ ለክልል ምክር ቤት አያቀርቡም ብሎ መምረጡም እውነትነቱ ከፀሐይ የበራ፣ ከውኃ የጠራ መሆኑን ማንም አይስተውም፡፡ እያንዳንዱን ግለሰብ በተናጠል መርምሮማ ቢሆን እንደልደቱ አያሌው ያለውን የውስጥ

አርበኛ፣ እንደነሙሴ ሰሙና አየለ ጫሚሶ ዓይነቶችን ከሃዲዎች አበጥሮና አንጠርጥሮ ወደ ትቢያ ይደፋቸው ነበር። ሥልጡኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ የደረሰበትን መከራና ስቃይ፣ ወከባና እንግልት ችሎ ያለምንም ማወላወል በዲሞክራሲያዊ ይዘት አምኖ መሪዎቹን በካርዱ መርጧል፤ አለምንም ማወላወል ድምጹን ተነጥቋል! ይህ ያገጠጠ፣ ያፈጠጠ እውነት ወዴትም ሊወሰድ፣ ሊሸፋፈንም ሆነ ሊበወዝ አይችልም። በቅቷል!!

ሕዝብ ፈልጎ፣ ወድዶ፣ አምኖና ፈቅዶ የመረጣቸውን ሀቀኛ የቅንጅት መሪዎችና የሕዝብ እንደራሴዎች እሥር ቤት አጉሮ ሌሎች መሪዎች ‹መረጥንልህ፣ አነኘኸውልህ፣› ማለት በሕዝብ ላይ ከማላገጥ ውጪ ሌላ ሊሆን አይችልም። ለሕዝብ የተለመደ ንቀትን ከማሳየትና ትዕቢተኛነትን ከማስመዝገብ ውጪ አንዳችም ፋይዳ አይኖረውም። እነአየለ ጫሚሶንና እነሙሴ ሰሙን አውገርግሮ ቅንጅት የሚል አዲስ ጥብቆ ማልበስ የቀድሞዎቹንና ሀቀኞቹን በምንም ሁኔታ ሊተካ የማይችል መሆኑን አሜሪካዊቷም ሆኑ ኢህአዴግ ሊገነዘቡት፣ ሊቀበሉትና ሊያምኑት የሚገባ ጉዳይ መሆኑን ስመ እግዚአብሔር ጠርተን ማሳወቅ እንፈልጋለን። በምንም ተዓምር የነአቶ አየለ ጫሚሶ ቅንጅት ተቀባይነት አይኖረውም፤ እንደተለመደው በግድያና በደም ታጅቦ እመኑኝ ካላለ በስተቀር። ይልቁኑ እውነተኛ መፍትሔው ቀላልና ግልጽ የሆነ ነው፤ ቅንጅት መንግሥትም ሆነ ምርጫ ቦርድ አወቀው አላወቀው በሕፃናት፣ ባዛውንቱ፣ ባጠቃላይ በህዝበ ኢትዮጵያ ልብና ሕሊና ውስጥ ሊፋቅ በማይችልበት ሁኔታ ታትሟል፤ ሊጠፋ በማይችልበት ኃይል በርቷል። ስለዚህ የማይሆንና የማያዋጣ ትርምስ ከመፍጠር መታቀብ ይበጃል እንላለን። ሰሚ ቢገኝ የሚበጀው መሪዎቹን መፍታት - ለይቅርታና ለዕርቅ ራስን ማዘጋጀት!! በቃ!!

የአሜሪካ ኤምባሲ ጉዳይ ፈጻሚዋ ‹ዲሞክረሲ ከውስጥ ሲመጣ እንጂ ከውጪ ሲጫን ውጤታማ አይሆንም› እንዳሉት በኢትዮጵያ ለአንድ ዓመት ያህል የተሰነካከለውን ዲሞክራሲያዊ ሂደት ለማስቀጠል እውነት ቢታሰብ ኖሮ፣ ቢሆንማ ኖሮ፣ ለኢትዮጵያ ስቃይና መከራ ማብቂያ፣ ለተፈላጊውም ዲሞክራሲ ማበብ ሀቀኛ ፍላጎትና ተነሳሽነት ቢኖር ኖሮ፣ ‹... የዕውሩንም ዓይን ትከፍት ዘንድ፣ የተጋዘውንም ከግዞት ቤት በጨለማም የተቀመጡትን ከወህኒ ቤት ታወጣ ዘንድ ለሕዝብ ቃል ኪዳን ለአሕዛብም ብርሃን አድርጌ እሰጥሃለሁ። ... › (ኢሳያ. ምዕ. 42 ቁ. 6-7)፤ ‹የተበደለውን ሰው ከሚበድለው ሰው እጅ አድነው፤ ለርሱም መፍረድ ቸል አትበል› (ሲራክ ምዕ. 4 ቁ. 9) እንደሚለው ቅዱስ ቃል በተሠራ ነበር። አዛውንቶች ታሥረው፣ እናቶችና ሕፃናት ተገድለው፣ ድምጻቸውን ለቅንጅት የሰጡ በገጠር በከተማ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በእየዕለቱ በሚዋከቡበትና በሚሰቃዩበት አገር ውስጥ በደል እንዲቀር፣ ፍርድ እንዲሚላ፣ ሰላም እንዲሰፍን የሚያደርግ ጥረት ከወዳጅ የሚጠበቅ ነበር። ቢያንስ የተከበሩ አና ጎሜዝን ያህል፣ የተከበሩ ኮንግረስማን ክርስቶፎር ስሚዝን ያህል፣ እዚህም እውስጥ ያሉት ከኢህአዴግ ጠ/ሚ ጋር ዕለት በዕለት የሚገናኙት ጉዳይ ፈጻሚ በሞከሩ ነበር። በሰበብ አስባቡ ለኢትዮጵያ በሚሰጥ እርዳታና ብድር የኢትዮጵያ ድሃ ያልተጠቀመ መሆኑንም፣ እንዲያውም በአሜሪካ ድጋፍ በተገኘ መሳሪያና መኪና ኢትዮጵያውያን እንደሚሳደዱበትና እንደሚገደሉበት ባለፈው ጥቅምትና ሕዳር ራሳቸው ጉዳይ ፈጻሚዋ በአደባባይ የመሰከሩት እውነት ነበር። ‹ባለጠጋ ድሆችን ይገዛል፣ ተበዳሪም የአበዳሪ ባሪያ ነው።› (ምሳሌ ምዕ. 22፣ ቁ. 7) እንደሚለው መፅሐፉ እንድናምን እየተገደድን መሆናችን ቢታወቅልንም ተገቢ ነው እንላለን። ይህ አልሆንላቸው ካለ ደግሞ የእኛኑ የውስጥ ጉዳይ ለእኛው ቢተውልንና እንዳፈተተን ብንሆን ይበጀን ነበር፤ የጠላት ቁጥር ከማባዛት ቢታቀቡልን እንደረዱን፣ እንደደገፉን እንቆጥርላቸው ነበር። ኢትዮጵያውያን እንደሆንን በምንም ተዓምር ከግንቦት ዘጠና

ሰባት በፊት ወደነበረው ህይወታችን አንመለስም፡፡ በጸሎትም፣ በሰላምም፣ ሆነ በሚያመችን መንገድ ብለን የነጻነታችንን ቀን እናዋልዳታለን፡፡

በሶስተኛ ደረጃ የምናነሳው ነጥብ አምና ከግንቦት ሰባት በፊትም ሆነ በሁዋላ በነበሩ የተቃዋሚዎች የስብከትና የማብራሪያ ንግግሮች ውስጥ ተደጋግሞ ይነገር ስለነበረው ‹ብርቱካናማ አብዮት› ጉዳይ ነው፡፡ እንደምናስታውሰው የብርቱካናማን አብዮት ሀሳብ ወደተቃዋሚዎች አጀንዳ የጨመሩት አቶ በረከት ስምኦን የዶ/ር ነገደ ጎበዜን መጽሐፍ ባስተዋወቁበት ወቅት ነው፡፡ ሰላማዊ እምቢተኛነት፣ አልገዛም ባይነት በማንኛውም መስፈርት የዲሞክራሲያዊ ትግል ዓይነተኛ መገለጫው መሆኑ ቀርቶ ኀጢአት ሆኖ በተወገዘበት ጊዜ ማለት ነው - በበረከት ስምኦን እይታ፡፡ እና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በአንዳንድ ንግግሩ ላይ አቶ ልደቱ አያሌው ያነሳሳው እንደነበረ ሁሉም ሰው የሚያስታውሰው ይመስለናል፡፡ ከእሱ ውጪ ሌሎች የተቃዋሚ ድርጅቶች አባላት አንድም ቀን ሲጠቅሱት የሰማንበት ዕለት ትዝ አይለንም፡፡ እዚህ ላይ ቢጠቅሱት ስህተት ይሆኑ ነበር ለማለት እንዳልሆነ ይታወቅልን፡፡ እና አቶ ልደቱ በጠቀሰውና በተናገረው የሁሉም የተቃዋሚ በተለይ ደግሞ የቅንጅት አቋም ተደርጎ ሲወቀሱበት እንሰማለን፡፡ ‹ላም ባልዋለችበት ኩበት ለቀማ› እንዲሉ ‹ብርቱካናማ አብዮትን› ካለፍ አገደም የለፈፈው አቶ ልደቱ፣ ባልተመረጠበት ድርጅት ስም ፓርላማ ገብቶ በሚያሽቃብጥበት ሁኔታ ውስጥ ጠ/ሚ መለስ ሌሎቹን መውቀሻ፣ መክሰሻ ለማድረግ መሞከራቸው ተሸፋፈኑ ላሞኛችሁ ዓይነት የልጆች የባውቅዮሽ ጨዋታ ከመሆን የሚያልፍ እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል እላለሁ፡፡

ዝግጅታችንን ጨርሰናል፤ ህዝቡን አነሳስተናል፤ ኢህዴግን በህዝባዊ አመጻ እናስወግደዋለን የሚል መልእክት እያስተላለፈ፣ ኢህአዴግም እሱን እየጠቀሰ ሌሎቹን ሲያጠቃበት የነበረውን ሀሳብ የሰነዘረውን ግለሰብ - አቶ ልደቱን- አቅፎና ደግፎ፣ በፓርላማም ያልተመረጠበትን ድርጅት ስም ሰጥቶ (አፈ ጉባኤ ተሸመ ቶጋ አቶ ልደቱን ኢደፓ መድህን ተወካይ እያሉ ሲጠሩት በቴሌቪዝን አይተናል፡፡ አቶ ልደቱ በቅንጅት ስም እንጂ በኢደፓ መድህን ስም አለመመረጡን መቼም ከእሱና ከኢህአዴግ በስተቀር የማያውቅ የለም፡፡) ተንከባክቦ እያለ ሌሎቹን አዛውንት ተመራጮችና መሪዎች መክሰስና መውቀስ አይን ያወጣ አጭበርባሪነት እንጂ ሌላ ሊሆን ከቶ አይችልም፡፡

ስለዚህ ያለንበት ያገጠጠ እውነታ ይኸ ሆኖ ሳለ ወዲያና ወዲህ ማለቱ በሰው ቁስል እንጨት ስደዱበት የሚለውን ብሂል የሚያልፍ ነው፡፡ እሚነደው ላይ ቤንዚን ማርከፍከፍ ቢሉትም ያስኬዳል፡፡

በአጠቃላይ ኢህአዴግም ሆነ የአሜሪካ ጉዳይ ፈጻሚ፣ ተለጣፊውን ቅንጅትን እሚያደራጁና ኢትዮጵያወያንን ለመምራት ያሰፈሰፉ ግለሰቦች ረጋ ብለው እንዲያስቡ የምንፈልገው ቅንጅት ማለት አምና በምርጫ ዘጠና ሰባት የተሳተፈው፣ መሪዎቹም በመስከረም አሥራ አራት የተመረጡትና በእሥር ላይ ያሉት ብቻ መሆናቸውን ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ትርፉ ትዝብትና ዘጥዘጥ ነው፡፡ ቀጥሎ እላይ ጠቀስ ያደረግነውን ግጥም ሙሉ ስንኖች አቅርበን ነገራችንን እንቋዋጫለን፡፡

- ሰው አልተፈጠረም -

እንዳይጥ በጉድጓድ በጨለማ እንዲኖር፤
ሳይሞት፣ ሳይገነዝ በቁሙ እንዲቀበር፤
በፍርሃት፣ በጭንቀት፣ በስጋት ለመኖር፤
ሰው አልተፈጠረም፤ ክርስቶስ ይመስክር!

መቃብር አይሞቅም፤ኑሮም ሊሆን አይችል፤
ሥጋውስ ይፈርሳል፤ ምስጥ ይመገበዋል፤
ነፍስንና አእምሮን በመቃብር ማዋል፤
ውርደት ነው፤ ቅሌት ነው፤ መጨረሻው ወንጀል!
ባራት እግሩ እንዲሄድ፤ አፈሩን እንዲግጥ፤
እያነፈነፈ እንደውሻ እንዲሮጥ፤
ሰውነቱን፣ ክብሩን በሆዱ እንዲለውጥ፤
ሰው አልተፈጠረም፤ እንዲኖር በቅልውጥ!
በተወለደበት በአደገበት ‹ዕድል›
እጆቹን አጣምሮ ስቃይ እንዲቀበል፤
ከጥሬ ሳይወጣ እንዲሞት በቅማል፤
ሰው አልተፈጠረም፤ ለዚህ ‹ዕድል› በደል!
ከሥጋ እሚወለድ ተባይ ለመመገብ፤
አንጀቱ ደርቆበት፤ እሱ ራሱ ሳይጠግብ፤
እውቀት እያነሰው፤ አንጎሉ እንዲደድብ፤
ሰው አልተፈጠረም እንደዚህ ላለግብ!
ቀና ብሎ እያየ ቀና ብሎ እንዲሄድ፤
በአእምሮ፤ በመንፈስ እንዲያድግ፤ እንዲራመድ፤
እየተሻሻለ ትውልድ ከትውልድ፤
እንዲገሠግሥ ነው ሳይቆም ሳይታገድ!
የእግዚአብሔር እስትንፋስ ነፍስና አእምሮው፤
በሥላሴ አርአያ ሆኖ የተሠራው፤
ከመልአክ በላይ ነው ሰውስ በተፈጥሮው፤
መንፈሱን አርክሶ ክብሩን ካልገፈፈው!
(ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም፤ 1967፤ እንጉርጉሮ። ገጽ 10)

አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን
ከአዲስ አበባ፤ ሚያዝያ 6 ቀን 1998 ዓ.ም.